# እንዴት አልታየውም!

ያ አዲሱ ገበሬ
አንቱ የተባለው
ገደብ ሳያስቀምጥ
ምነው አቃጠለው እሣር ቁጥቋጦውን፤
እንዲት አልታየውም
ዝናቡ ሲዘንብ
ከአፈር ጋር ጠራርጎ
ጎርፉ እንደሚወስደው ክረምት የዘራውን።

## እንዴት አልታየውም!

አገሬ ኢትዮጵያ
እስኪ ልጠይቅሽ
ክረምት እንዲህ ደርሶ
ዘር የሚዘራበት
በሮቹ አለቁ ወይ ወስኮ የሚስቡት፤
አዲሱ ገበሪ
እርፍ ከመያዝ ይልቅ ሲቆፍር አየሁት።
አዲሱ ገበሪ
የመሪቱ ጠባይ ምነው አልገባውም
ሞፈር ቀንበር ጥሎ
እንዲት ሊዘልቀው ነው ያን ማሳ ቆፍሮ፤
እንኮን እርሻን ያክል አይዘራም በጎዋሮ።

## እንዴት አልታየውም!

በሮቹ እንኮዋን ቢያልቁ
አዲሱ ገበሪ

## እንዴት አልታየውም

በሬ መከራየት
በኢትዮጵያ መሪት
በሞኘነት ይሆን ወይስ ለይስሙላ
በቁፈራ ማሣ፤
ሊዘራ ተነሣ።

## እንዴት አልታየውም!

አዲሱ ገበሪ
አፈር ሳይመረምር
ማዳበሬያ አልብሶ
ክረምት የዘራውን
ልምም ሆነ ጥሪ ቶሎ ያበቀለው፤
ይንጨሆረር ጀመር ድርቅ እንዳቃጠለው።

## እንዴት አልታየህም!

አዲሱ ገበሪ
እባክህ አዳምጠኝ፤
ምክር ልለግሥህ
አንተም ባትጠይቀኝ።
ሲሉ ሰምቻለሁ አገር ቤት አልጠፋም
አፈርና ዘሩን በደንብ የሚያውቀው፤
ጥሩ እህል ለማምረት
ነውር አይምሰልህ እባክህ አማክረው።

## እንዴት አልታየህም!

አንተ አዲስ ገበሪ
እሱን በመጠየቅ እውቀት ካልገበየህ፤
እንኮዋን ክረምትና በጋም ትራባለህ።

## እንዴት አልታየህም!

እርሃቡስ ባህል ነው
ብለህ ከተሞአገትህ በአትዮጵያ መሬት፤
ታሪክ ይወቅስሃል
ለእሳር ለቁጥቆዋቹ ሲል በከንቱ ላለቁት።

አዲስ የሐገር አስተዳደር እንተልምልህለን ያም አስተዳደር ከብዙ አንዱ መብትህን የሚያስጠብቅ ይሆናል ካሉ በሆዋላ የሰጡትን ቃል ለሚያጥፉ ሁሉ ማሳሰቢያ የተጻፈ ነው።

ለምለም ጸጋው፤ December 16, 2007